# አዚኦን አቡነ ጳውሎስ!!



በደጋጎች ወንበር ያልተቀመጠ!!

**መንገዱ የዋዘኞች፣ የክፎዎቹ መስመር ፣**

**በዋዛ ቆብ ደፍቶ ፣ እንደዚህ ሊሰበር ፣**

**መስቀሉን ለውጦ ፣ ሽጉጥ የተኮሰ፣**

**ሕግህን የተው ፣መነኩሴ ያስለቀሰ ፣**

በቁመናው ሳለ ፣ ሃውልቱን የሰራ ፣

ከንቱ ውዳሴ የሚወድ ፣ ለሰው የማይራራ፣

የሚበላ ጠፍቶ ፣ የሚቀመስ ዳቦ ፣

ሃውልቱን ያቆመ ፣ ሕፃናት አስርቦ ፣

በንጹሕ በፍታ ፣ ስጋው አይከፈን ፣

መቃበሩ ይብላው ፣ የሕዝብ ሁሉ ሃዘን ፣

ይንከባለልበት ፣ ትልቅ ድንጋይ ይጫን::

መቅደስ ያረከሰ ፣ መዓት የወሰደው ፣

ሕግህን የጠላ ፣ዘመኑ እንደሳር ነው !!

**በዐመፃ የተፀነስክ ፣ በኀጥያት የተወለድክ ፣**

**በሕዝቡ የጨከንክ ፣ ዋልድባን የደፈርክ ፣**

**ዐመፃ መንገዱ ፣ በልቡ ሃሳብ ኮርቶ ፣**

**ለታረዙት ሳይሆን ፣ ለበዳይ ሞግቶ ፣**

ሕግጋት ያዛባ ፤ ትእዛዝ ያልጠበቀ ፤

በሚበላ እሳት ፤ ይኸው ተነጠቀ ፡፡

ሁሉ በእርሱ ሆነ ፤ መድሃኒት ሆነልኝ ፤

ሕግ ተላላፊውን ፤ ፈጥኖ ቀሰፈልኝ ፤

ከመንበሩ አዋርደህ ፤ ካፈር ደባለከው ፤

ልቡ የጠመመ ፤ ዘመኑ እንደሳር ነው ፡፡

እግዚአበሔር እግዚእ መስተበቅል::

እግዚአበሔር መስተበቅል ገሃደ::

እግዚአብሔር የበቀል አምላክ ነው::

የበቀል አምላክ ተገለጠ::



መይሳው ከምድረ ስዊድን

2012-08-18